የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ኅዳር 1/2004

# ማሳሰቢያ

## መብት ለእኛ በደል ለነሱ አያዋጣም !

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ማለትና ሉሁሉም መፈታት መታገል ሲገባ “ የእኛ እስረኞች” የሚል አጓጉል ፈሊጥ ሰፍኖ መብት ለእኛዎቹ ሌሎቹ ግን ይማቅቁ ዓይነት አቀዋም በመንፀባረቁ የሰብ ዓዊ መብት ትግላችን ስንኩል የሆነበት ሁኔታ ሰፍኗል።

በቅርቡ 18 ዓመት በህገ ወጥ መንገድ ታስሮ የተፈታው አቶ አበራ የማነአብ አንድ ምሳሌ ነው። በአቶ አበራ የፖለቲካ አቀዋም የተነሳ ብዙዎች መታሰሩን አንዲትም ቀን ሳይቃወሙ ዓመታት አልፈዋል። አምኔስቲ ኢንተርናሽናል የተባለው ተቋም ለምሳሌ በኢፖእአኮ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም የአቶ አበራን በግፍ መታሰር መቃወም አልፈለገም። የውጮቹም ሆኑ የውስጡ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቀዋሞች በወያኔ ታስረው የጠፉ የኢሕአፓ መሪዎችና አባላትን ጉዳይ ከቶም አናነሳም እንዳሉ አሉ። አባሎቻችን ታሰሩ ብለው የሚጮሁ የብሄረሰብ ድርጅቶች ለምሳሌ ከራሳቸው ውጪ ማንም ቢታሰር ማን ድምፃቸውን ከቶም አያሰሙም። ሰብዓዊ መብትና ፖለቲካ አቀዋምን መደበላለቁ ስህተት እየሆነ ሳለ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ነን እያሉ ግን ለሁሉም የተበደለ ዜጋ ሰብዓዊ መብት መረገጥ ቃዋሚና ተሟጋች መሆን ያቃታቸው ጥቂቶች አይደሉም። ታስረው ሳለ የተጮኸላቸው እስረኞችም ቢሆኑ ሲፈቱ ለሁሉም የፖለቲካ እስረኞች መፈታት መጮህ መታገል ሲገባቸው ይህን ሲያደርጉም አልታዩም። ወያኔ በዚህ ደረጃ ብልጥ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳዲስ እስረኞች ሲያፍን ሲያግዝ እነዚህን ብቻ በሚል የሚደረገው ጩኸት ሌሎችን እያስረሳ ሄዷል። ይህም ለወያኔ ያመቸዋል። ከ1983 እስከ 1997 ዓ.ም. ያሰራቸውን በ1997 ኡ ባጎራቸው አስረስቷል። በዚህ ጊዜም ቢሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በዴዴሳ፣ዝዋይ፣ ብር ሸለቆ ወዘተ ታስረው ሲሰቃዩ ትኩረቱ የነበረው ከርቸሌ በገቡ የግንባር መሪዎች ላይ ብቻ ነበር። ዛሬም ቢሆን ሺዎቹ ተረስተዋል። አንድ ቀን አንዱን አንዷን አስሮ ሲፈታ በዚሁ ድንግርግር እየሰፈነ ሌሎች ደግሞ ሲታፈሱ ጩኸቱ ለነዚሁ ብቻ ይሆናል።

ሁሉም ማለት ሁሌም ለሁሉ መጮህ ከባድ ሆኗል፡፡ ይህበጊዜ መታረምና ሁላችንም መብት ሲረገጥ መቼም ቢሆን ማን ህግ ወጥ ነው ብለን መቃወም ይገባናል፡፡ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ሲባል ም በተጨባጭ ሁሉን ማለቱንም በተግባር ማሳየት ይገባል፡፡ አንዳንዶች ስለተደረጉ ሰልፎች እንኳን ሲዘግቡ “የነሱ ” ያልሆኑ የፖለቲካ እስረኞች ፍቶዎችን ወይም ሰሌዳዎችን ቆርጠው ሲተዉ ታዝበናል፡፡ ዘገባቸውን ያለተሟላ መሆኑን በተደጋጋሚ ያደመጥ ነው፡፡ የሚያሳዝንም ነው! በሀገራ ችን ሰብዓዊ መብት ሲረገጥ ተጠቂው ያለው የፖለቲካ አቅዋም ሳይሆን ዋናው ጉዳይ ዜጋ ሆኖ መብቱ መነፈጉ መረገጡ ነው ተቃውሞን ከሁሉም መጋበዝ ያለበት፡፡ ፖለቲካ እስረኞችን የእኛ የነሱ ብሎ መፈረጅ በጣም ስህተትና መቆምም ያለበት ነው፡፡

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!

መብታቸው የተረገጠ ዜጎች ሁሉ የእኛ ናቸው!

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE